# ተቋማት ኤች አይቪን ለመከላከል
# የመደበቡት በጀት የአጠቃቀምና የአፈፃፀም መመሪያ

## የአብክመ ኤች አይቪ ኤድስ
## መከ/መቆ/ማስተ/ጽ/ቤት

መጋቢት 2002.ዓ.ም
ባሕር ዳር

## መግቢያ

የኤች አይ ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ ከ30 ዓመት በላይ ሆኖታል:: በእነዚህ ዓመታት ወረርሽኙ በዓለም ደረጃ ከ30 ሚሊየን ለሚበልጡ ሰዎች የሞት ምክንያት ሲሆን በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ከ 33.4 ሚሊየን በላይ የሚሆኑ ሰዎች ኤችአይ ቪ በደማቸው ውስጥ እንደሚገኝ ይገመታል:: ከነዚህም ውስጥ ከሃያ ሁለት ሚሊየን በላይ ወይም ሁለት ሦስተኛው የሚሆኑት ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ የሚኖሩ ናቸው::

በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒሰትር የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት በተገኘው መረጃ መሰረት በአገራችን በ2002 ዓ.ም 1,216,908 ወገኖች ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ እንዳለ ይገመታል:: የኤች አይ ቪ ሥርጭት በአማካይ 2.4 ከመቶ ሲሆን ሥርጭቱ በከተማ 7.7 ከመቶ፤ በገጠር ደግሞ 0.9 ከመቶ እንደሆነ መረጃዎች ያሣያሉ:: ኤችአይቪ በደማቸው ውስጥ ከሚገኝ ወገኖች መካከል 397,818 የሚሆኑት የፀረ ኤችአይቪ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው እንደሆነ ይገመታል:: ወላጆቻቸውን በኤድስ ሳቢያ ያጡ 804,184 የሚገመቱ ሕፃናት ድጋፍና ክብካቤ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ:: በ2002ዓ.ም ብቻ 137,494 የሚጠጉ ወገኖች በኤችአይቪ እንደ ተያዙ መረጃው ያመለክታል::

በተመሳሳይ ወቅት በክልላችን የለውን ሁኔታም ስንመለከት በአሁኑ ወቅት 379,096 ወገኖች ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ እንዳለ ይገመታል:: ሥርጭቱም በአማካይ 2.9 ከመቶ ሲሆን በከተማ 9.8 ከመቶ፤ በገጠር 1.4 ከመቶ እንደሆነ የቅኝት መረጃዎች ያሣያሉ:: ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ ከሚገኝባቸው ወገኖች መካከል 126,066 የሚሆኑት የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው እንደሆነ ይገመታል:: ወላጆቻቸውን በኤድስ ሳቢያ ያጡ ወደ 318,220 የሚገመቱ ሕፃናት ድጋፍና ክብካቤ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ:: በ2002 ዓ.ም ብቻ 42,543 የሚጠጉ ወገኖች በኤች አይ ቪ እንደ ተያዙ ውጤቱ ያመለክታል::

የችግሩ ስፋት ከለጋሾች በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ ብቻ ሊቀረፍ የማይችል ስለሆነና መንግስታት የራሳቸውን ችግር በራሳቸው የመፍታት ኃላፊነት ስላለባቸው ከሰሀራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገሮች ከዓመት በጀታቸው 15% ኤችአይቪ/ ኤድስን ለመከ/መቆ/ ተግባር እንዲውል ወስነዋል::

ስምምነቱን ከፈረሙት ሀገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ናት፡፡ በስምምነቱ መሰረት ሀገራችን ያለባትን የበጀት እጥረት ከግምት ውስጥ በማስገባት ቢያንስ ከዓመታዊ የስራ ማስኬጃ በጀት 2 % እና ከዚያ በላይ ኤችአይቪ/ኤድስን ለመከ/መቆ/ ሥራ እንዲውል በመወሰኑ ከ1998 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡

ይሁን እንጂ አፈጻጸሙን በተመለከተ ግልጽ የሆነ መመሪያ ባለመኖሩ የበጀት አመዳደብና አጠቃቀም ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

በመሆኑም ችግሮችን ለመፍታት ይረዳ ዘንድ ይህ የአጠቃቀምና አፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል፡፡



# ክፍል አንድ ጠቅላላ

## አንቀጽ- 1

### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ተቋማት ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከ/መቆ/ ለሚመድቡት በጀት የአጠቃቀምና አፈጻጸም መመሪያ" ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

## አንቀጽ-2

### ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ኤች አይ ቪ" ማለት የሰውን በተፈጥሮ በሽታን የመከላከል አቅም የሚያዳክምና ለተለያዩ በሽታዎች የሚያጋልጥ ቫይረስ ነው፡፡
2. "ኤድስ" ማለት በኤች አይ ቪ ሳቢያ የሰውነት የመከላከል አቅም ሲዳከም የተለያዩ በሽታዎች ሰውን ሲያጠቁትና ስብስብ የበሽታ ምልክቶች በሰውነት ላይ ሲታዩ ነው፡፡
3. ተቋም ማለት፡- ህጋዊ አደረጃጀት ያለው በስሩ ሰራተኞችን ቀጥሮ የሚያሠራ በመንግስት፤መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤በማህበራትና በግል የተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡
4. "ሜይንስትሪሚንግ" ማለት ኤችአይቪኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባር ዋና የልማት አጀንዳ ማድረግ ነው፡፡/የተ.መ የልማት ፕሮግራም ትረጉም/
5. "ውስጣዊ ሜንስትሪሚንግ" ማለት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በተቋሙ ሠራተኞችና በቤተሰቦቻቸው ላይ ጉዳት እንዳያደርስና የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ የሚያስችል ስልት መንደፍና መተግበር ነው፡፡
6. "ውጫዊ ሜንስትሪሚንግ" ማለት ማንኛውም ተቋም የተቋቋመበትን ግብና ዓላማዎች ለማሳካት በሚያደርገው አጠቃላይ እንቅስቃሴ የተቋሙ ደምበኞች ወይም ተጠቃሚው ህብረተሰብ ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንዳይጋለጥ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግና ወረርሽኙን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ በማድረግ በህብረተሰቡ ውስጥ ማስረፅ ማለት ነዉ፡፡

7 "ተጠሪ ግብረ ኃይል" ማለት በአንድ ተቋም ውስጥ ለሚካሄደው የሜይንስትሪሚንግ ተግባር አስተባባሪ እንዲሆን ከሰራተኞች ተውጣጥቶ የሚቋቋም ቡድን ሲሆን የኤችይቪ ኤድስን ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ የተቋሙን እቅድ የማሳቀድና የማስፈፀም ተልእኮ ያለው ኃይል ማለት ነው፡፡

8 "ተጠሪ ባለሙያ" ማለት በአንድ ተቋም ውስጥ ለሚካሄደው የሜይንስትሪሚንግ ተግባር አስተባባሪ እንዲሆን ከሰራተኞች መካከል ሙሉ ጊዜውን ወይም በከፊል ጊዜውን መድቦ የሚሰራ ሰራተኛ ሲሆን የኤችአይቪ/ኤድስን ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ የተቋሙን እቅድ የማሳቀድና የማስፈፀም ተልእኮ ያለው ባለሙያ ማለት ነው፡፡

9 ማስፈጸሚያ በጀት፡- ተቋማት ኤችአይ ቪ ኤድስን ለመከላከል ከሥራ ማስኬጃ በጀታቸው የሚመድቡት በጀት ነው፡፡

## አንቀጽ -3

### ዓላማ

በክልላችን በሁሉም ደረጃዎች በሚገኙ ተቋማት ኤችአይቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠሩን ተግባር የመደበኛ ስራቸው አካል አድርገው አቅደው እንዲተገብሩ እና ለእቅዳቸው ማስፈፀሚያ የሚመድቡትን በጀት በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ ነው፡፡

## አንቀጽ- 4

### ዝርዝር ዓላማ

- የኤች አይ ቪ /ኤድስ ወረርሽኝ ዘርፈ ብዙ ምላሽ የሚያስፈልገው በመሆኑ በሁሉም ተቋማት የስራ ቦታዎች ወረርሽኙን የመከላከል ተግባር የመደበኛ ስራቸው አካል አድርገው እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ፡
- ተቋማት በኤች አይቪ ዙሪያ ውጤታማ የሆነ እቅድ እንዲያቅዱ ለማድረግ፡
- በየደረጃው ያሉ ተቋማት ኤች አይ ቪን ለመከላከል ስለሚመድቡት በጀት አጠቃቀም የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ፡፡

## አንቀጽ -5

### አስፈላጊነት

- የተቋማት የፀ-ረኤችአይቪ እቅድ የማቀድና የመፈጸም አቅም ይጎለብታል፤
- በጀት አመዳደብና አጠቃቀም ይታዩ የነበሩ ችግሮች ይወገዳሉ፤
- በአፈጻጸም ችግር ምክንያት በጀት ሳይመድቡ የቆዩ ተቋማት እንዲመድቡ ያግዛል፤
- ተቋማት ኤችአይቪኤድስን በመከላከሉና በመቆጣጠሩ ተግባር ላይ ባለቤትነታቸውን ያሳድጋል፡፡

# ክፍል ሁለት

## አንቀጽ- 6

### የኤችአይቪ/ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ዕቅድ ማዘጋጀት

6.1 ተቋማት በሰራተኞቻቸውና በደንበኞቻቸው ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ብሎም ለመከላከል የዋና ተግባራቸው እቅድ አካል በማድረግ አቅደው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡

6.2 የሚዘጋጀው እቅድ ከነባራዊ ሁኔታው ጋር የተጣጣመና ውጤት ሊያመጣ የሚችል መሆን አለበት፤

6.3 የኤችአይቪ/ ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር ተገባራት ለማቀድ የምንከተላቸው ስልቶች

6.3.1 የኤችአይቪ ኤድስ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ

☝ በዳሰሳ ጥናቱ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- ኤችአይቪ/ኤድስ እያደረሰው ያለ ተጽእኖ
- የፖሊሲና መመሪያዎች ምቹነት
- የመፈጸም አቅም
- የግብአት ፍላጎት

6.3.2. በተቋሙ ውስጥና ውጭ የኤችአይቪ ኤድስን ስርጭት ሊያስፋፉ የሚችሉ መንገዶችን መለየት፣

6.3.3 የተቋሙ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን መለየት፣

6.3.4. ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ችግሮችን መለየት፣

6.3.5. ለተለዩ ችግሮችና መፍትሄ ማስቀመጥ፣

6.3.6. የመፍትሄ ሃሳቦች ዝርዝር የአፈፃፀም ዕቅድ ማዘጋጀት፣

6.4. ተቋማት ዓመታዊ ዕቅዳቸውን በየደረጃው ላሉ የኤችአይቪ/ ኤድስ መከ/መቆ/ማስተ/ ጽ/ቤት ማሳወቅ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ -7

## በጀት ስለ መመደብ

7.1. ተቋማት ኤችአይቪ/ ኤድስን ለመከላከል ተግባር ዕቅድ ማስፈጸሚያ በጀት መመደብ አለባቸው

7.2. የሚመደበው በጀት ከዓመታዊ ሥራ ማስኬጃው 2% እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

7.3. ተቋማት በየዓመቱ ወይም በፕሮጀክት በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 7.2 የተጠቀሰውን በጀት ስለመመደባቸው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ መምሪያዎችና ጽ/ቤቶች ክትትል የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

7.4. ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና ጽ/ቤቶች ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው ተቋማትን በተመለከተ ተቋማቱ ላይ ክትትል የሚያደርጉ የመንግስት አካላት በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 7.2 የተጠቀሰውን በጀት መመደባቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

7.5. ተቋማት የሚመድቡትን በጀት በእቅድ የተደገፈና በየደረጃው ላሉ የኤችአይቪ/ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ -8

## ስለበጀት አጠቃቀም

8.1. በአንቀጽ7 በተራ ቁጥር 7.2 የተመደበው በጀት ኤች አይቪ/ ኤድስን የመከላከል ከዚህ በታች ለተጠቀሱት ተግባራት ሊውል ይችላል

- የመረጃና ትምህርት ስርፀት ቁሳቁስ ማዘጋጀትና ማሰራጨት
- የተቋማት መደበኛ የስራ ቦታ ውይይት ማከሄድ
- የሚኒሚዲያ ክበብ ማቋቋም
- የሠራተኞች ቋሚ የዉይይት መድረኮችን በማዘጋጀትና ባለሙያዎችንና ኤችአይቪ በደማቸው የለባቸው ሠዎችን በመጋበዝ የፓናል ዉይይቶችን ማዘጋጀት
- የአቻ ለአቻ ትምህርት ፕሮግራም ማዘጋጀት
- ስለ ጤና አገልግሎቶች ቅስቀሳ ማድረግና አገልግሎት መስጠት
    - የኤችአይቪ የምክርና የደም ምርመራና አገልግሎት ቅስቀሳ ማድረግና አገልግሎት አንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት
    - የኤችአይቪ የምክርና የደም ምርመራና
    - የኤችአይቪ ከእናት ወደ ፅንስ /ልጅ/ እንዳይተላለፍ የመከላከል አገልግሎትን ማመቻቸት
    - የፀረ-ኤችአይቪ መድሃኒት አገልግሎትና አጠቃቀም ቅስቀሳ
    - የአባላዘር በሽታዎች መከላከልና ህክምናና አገልግሎቶች ቅስቀሳዎች
- ኮንዶም ማስተዋወቅና ማሰራጨት
- አቅም ግንባታ
    - የባህሪ ለውጥ ስርፀት ስልጠና
    - የማህበረሰብ ውይይት ስልጠና
    - የህይወት ክህሎት ስልጠና
    - የአቻ ለአቻ ውይይት ስልጠና
    - የሜይንስትሪሚንግ ስልጠና

የአድቮኬሲ ስልጠና ና የመሳሰሉትን ስልጠናዎች ማካሄድ፣መስጠትና መሳተፍ

- ለትብብር መድረኮች ተሳትፎ
- ለዳሰሳ ጥናት
- ተቋማት የውስጥ መመሪያዎችና ደንቦችን ለማውጣት ወይም ለማሻሻል
- ለክትትልና ግምገማ

8.2 በሁሉም ተቋማት ውስጥ ከተለዩ ተግባራት መካከል ቅድሚያ ለውስጣዊ ሜንስትሪሚንግ አገልግሎት ማዋል ይገባል፡፡

8.3 የ 2% በጀት ጥቅም ላይ ሊውልባቸው የማይገቡ ተግባራት

- ለሌሎች ተቋማት ማስተላለፍ
- ለድጋፍና ክብካቤ ማዋል
- ከኤችአይቪ ኤድስ መከላከል ተግባራት ውጭ መጠቀም
- ከፀረ-ኤድስ ፈንድ ማሕበር ጋር አደባልቆ መጠቀም

## አንቀጽ- 9

## ተጠሪ፣ ግብረ-ኃይል ወይም ባለሙያ ስለመመደብ

9.1. ሁሉም ተቋማት አንደየተቋሙ አደረጃጀት ስፋትና ጥበት እንደየ የሰው ኃይሉ ብዛት የኤችአይቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጣር ተግባራት በተቋሙ ውስጥ በሚገባ መታቀዳቸውንና አፈፃፀማቸውን የሚከታተል የኤችአይቪ/ ኤድስ መከ/መቆ/ ሥራዎች ተጠሪ ወይም ግብረ-ኃይል ወይም ባለሙያ መመደብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

9.2. ለኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሥራዎች በተጠሪነት የሚመደበው አካል ለዚህ ሥራ የተመደበለት ጊዜ መጠን ሙሉ ወይም ከፊል ሊሆን ይችላል፡፡

9.3. የተመደበው ጊዜ በከፊል ከሆነ የጊዜው መጠን ተለይቶ ሊቀመጥና በዚያው መጠን ሊመዘን ይገባል፡፡

## ⚜ አንቀጽ - 10 ⚜

## *ክትትልና ግምገማ*

10.1 ዕቅድና ሪፖርቶችን ማዘጋጀትና በየደረጃው ላሉ የኤችአይቪኤድስ መከ/መቆ/ማስ/ጽ/ቤቶችና ለሚመለከተው አካል ማቅረብ

10.2 በመደበኛ የሩብ ዓመት ግምገማዎች ላይ አፈፃፀሙን አብሮ መገምገም

10.3 ውሳኔ ሰጭ/አመራር አካላትን በፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ላይ ማወያየት

10.4 ተጠያቂነት እንዲኖር፣ በውጤት ተኮርና በዋና ፕሮግራሞች እንዲካተት ማድረግ

10.5 ሞዴል ሊሆኑ የሚችሉ ስራዎችን ማሳዬትና አርአያ መሆን

10.6 የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ማዘጋጀት

10.7 በተዋረድ ላሉ ተቋማት ድጋፍና የክትትልና ግምገማ ስራዎችን መስራት

## ⚜ አንቀጽ - 11 ⚜

## *የበጀት አርዕስትን በተመለከተ*

በገንዘብና ኤኮኖሚ ቢሮ ስር ባለ በጀት ለሚተዳደሩ ሴክተሮች በበጀት ማሻሻያ ማንዋሉ ክፍል አንድ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር መሠረት ሆኖ፡-

ሀ. የሚሰራው ስራ በዚህ መመሪያ ስር በተጠቀሱ የበጀት አርእስት ስር ይመደባል፡፡ ምሳሌ የታቀደው ስራ ለሰራተኞች ስልጠና መስጠት ከሆነ የወጭ መደቡ “አገር ውስጥ ስልጠና” ሆኖ መለያ ቁጥሩ /ኮዱ/ 6271 ይሆናል፡፡

ለ. የታቀደው ስራ በመመሪያው ውስጥ ከተጠቀሱት የወጭ መደቦች ጋር የሚጣጣም ካልሆነ ልዩ ልዩ ክፍያዎች በሚለው የወጭ መደብ ውስጥ የሚካተት ሆኖ መለያ ቁጥሩ 6419 ይሆናል፡፡

# ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ

### አንቀጽ -12

***የኤችአይቪ ኤድስ መከ/መቆ/ማ/ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት***

በየደረጃው ያሉ የኤችአይቪ ኤድስ መከ/መቆ/ማ/ጽ/ቤቶች በዋነኛነት የኤችአይቪ ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር ተግባራት ለማስተባበር፤ ክትትልና ግምገማ ለማካሄድና ሀብት ለማፈላለግ በመሆኑ በተቋማት ውስጥ ያለውን የሜንስትሪሚንግ ተግባራት አፈፃፀም መከታተልና ማስተባበር ይጠበቅባቸዋል፡፡

### አንቀጽ -14

***የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን***

ይህ መመሪያ በአማራ ብሄራዊ ክልል ውስጥ ባሉ ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ - 15

***መመሪያውን ስለማሻሻል***

ይህን መመሪያ ለማሻሻል ካስፈለገ የአብክመ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ማስ/ጽቤት ስልጣን ይሆናል፡፡

### አንቀጽ - 16

***መመሪያው ተግባራዊ ስለሚሆንበት ጊዜ***

ይህ መመሪያ በአብክመ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ማስ/ጽ/ቤት ፀድቆ ከወጣበት ከግንቦት 1 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡